https://t.me/Ethiopian_Digital_Library

ምዕራፍ 1

ሰላምታ በቻይንኛ

https://t.me/Ethiopian_Digital_Library

አዳዲስ ቃላት

የቻይንኛ ካራክተር	የፒንይን አነባብ	የአማርኛ አነባብ	ትርጉም
你	nǐ	[ኒ]	አንተ/አንቺ
好	hǎo	[ሀው]	ጥሩ/ደህና
您	nín	[ኒን]	እርስዎ (የአክብሮት አጠራር)
你们	nǐ men	[ኒመን]	እናንተ
谢谢	xiè xiè	[ሺዬ ሺዬ]	አመሰግናለሁ
不客气	bú kè qì	[ቡ ከ ቺ]	ምንም አይደል
再见	zài jiàn	[ዛይ ጂየን]	ቻው/ደህና ሁኑ

ቻይናዊያን ሰላምታ ሲለዋወጡ “你好/ní hǎo/ኒ ሀው” ይባባላሉ። ከላይ ያለውን ሰንጠረዥ እንደምታዩት “你/nǐ/ኒ” ማለት “አንተ” ወይም “አንቺ” ማለት ነው። “好/hǎo/ሀው” ማለት ደግሞ “ጥሩ” ወይም “ደህና” ማለት ነው። ሁለቱ ሲገናኙ “ኒ ሀው” የሚል አረፍተ ነገር ይመጣል። ይህ ማለት “አንቺ/አንተ ደህና?” እንደማለት ነው። እንደሰላምታ ይጠቀሙበታል። አንድ ሰው “你好/ní hǎo/ኒ ሀው/” ሲሎት እርስዎም “你好/ní hǎo/ኒ ሀው/” ብለው ነው የሚመልሱት።

አንድ ልብ እንድትሉ የሚገባችሁ ነገር አለ።“你好/ní hǎo/ኒ ሀው” የሚለው አረፍተነገር ሲመሰረት የ“你/ní/ኒ” ቶን ከሶስተኛው ወደ ሁለተኛው ቶን ተቀይሯል። ይህም የሆነበት ምክንያት በቻይንኛ ሁለት ቃላት ሶስተኛ ቶንን ይዘው

https://t.me/Ethiopian_Digital_Library

ተከታትለው ሲቀርቡ ውበት ያንሳቸዋል፤ ለተናጋሪውም ያስቸግራሉ ተብሎ ነው። ስለዚህ የመጀመሪያው ቃል ቶኑን ወደ ሁለተኛው ቶን ይለውጣል። አሁንም ይህ ሊያሳስባችሁ አይገባም። ልምድ ባካበታችሁ ቁጥር እየቀለላችሁ ይመጣል።

እስቲ አሁን ደግሞ "ሰላም ናችሁ?" እንዴት እንደሚባል እንማር። "你nǐ/ኒ" ለአንድ ሰው ሲሆን "你们/nǐ men/ኒ መን" ደግሞ ለብዙሃን ነው። "እናንተ" እንደማለት ነው። በነገራችን ላይ "们/men/መን/" አንድን ቃል ሲከተል እንደ የብዛት ማመልከቻ ያገለግላል። በአማርኛ "ሰው" ላይ "ዎች" ብንጨምር ብዛትን እንደሚያሳይ ሁሉ በቻይንኛም "们/men/መን/" የሚለው ቃል ብዛትን ይገልፃል። ስለዚህ "你们好/nǐ men hǎo/ኒ መን ሀው" ስንል "እናንተ ደህና?" ወይም "ሰላም ናችሁ?" እንደማለት ነው። "们/men/መን" የሚለውን ቅፅል የምንጠቀመው ከሰው ወይም ከህዝብ ጋር ግንኙነት ሲኖረው ነው። ለምሳሌ "መኪኖች" ለማለት ይሄንን ቅፅል አንጠቀምም።

ቻይንኛ ልክ እንደአማርኛ የአክብሮት ጥሪም አለው። በአማርኛ ያው "እርስዎ" ነው የምንለው። በቻይንኛ ደግሞ "您/nín/ኒን" ነው የሚባለው። እስቲ "ደህና ኖት?" እንዴት እንደሚባል ገምቱ። "您好/nín hǎo/ኒን ሀው" ካሉ በትክክል መልሰዋል!

ምስጋናን ለመግለፅ "谢谢/xiè xiè/ሺዬ ሺዬ" እንላለን። በፒንይን "xiè xiè" ስንል ከ "ሲ" እና ከ "ሺ" ማህል ያለን ድምፅ ነው የምናሰማው። ይህንን ድምፅ ለመስማት የድምፅ ቅጂውን ይከተሉ።

https://t.me/Ethiopian_Digital_Library

ማሳሰቢያ

አንድ ሰው ሲያመሰግኖት ደግሞ “不客气/bú kè qì/ቡ ከ ቺ” ብለው ይመልሳሉ። “不客气/bú kè qì/ቡ ከ ቺ” ቃል በቃል ሲተረጎም “እንደዚህ አይነት አክብሮት አይገባም” የሚል ትርጉም አለው። ይህ ደግሞ የሰዎቹን ቅርበት ያሳያል። ከሁለት በጣም የሚቀራረቡ ሰዎች መሐል እንደዚህ አይነት ስነስርዓት ወይም እጅ መንሳት አስፈላጊ እንዳልሆነ ነው የሚያመላክተው። እንግዲህ “ምንም አይደል” እንደማለት ነው። ልብ ያላችሁ እንደሆነ ይህች “不/bù/ቡ” የምትባለዋ ካራክተር አሁንም አለች። ቅድም እንደገለፅነው አፍራሽ ቃል ነች። “አይገባም” የሚለውን ትርጉም ለማስተላለፍ ነው የምንጠቀምባት።

በመጨረሻም “ቻው” ወይም “ደህና ሁኑ” ለማለት የምንጠቀምበት አባባል “再见/zài jìan/ዛይ ጂየን/” ነው። ይህ አባባል ቃል በቃል ሲተነተን “እንደገና እስክንገናኝ” የሚል ትርጉም አለው። “ዛይ ጂየን” ሲባሉ እርሶም “再见/zài jìan/ዛይ ጂየን/” ብለው ነው የሚመልሱት።

ልምምድ

https://t.me/Ethiopian_Digital_Library

	የቻይንኛ ንግግር	ትርጉም
A:	你好 [ኒ ሀው] ní hǎo	ደህና ነህ/ነሽ?
B:	你好 [ኒ ሀው] ní hǎo	ደህና ነህ/ነሽ?

C:	你们好 [ኒ መን ሀው] nǐ men hǎo	ደህና ናችሁ?
A,B:	你好 [ኒ ሀው] nǐ hǎo	ደህና ነህ/ነሽ?

https://t.me/Ethiopian_Digital_Library

A: 谢谢
[ሲዬ ሲዬ] xiè xiè
አመሰግናለሁ።

B: 不客气
[ቡ ከ ቺ] bú kè qì
ምንም አይደል።

A: 再见
[ዛይ ጂየን] zài jiàn
ቻው/ደህና ሁኑ።

B: 再见
[ዛይ ጂየን] zài jiàn
ቻው/ደህና ሁኑ።

https://t.me/Ethiopian_Digital_Library

https://t.me/Ethiopian_Digital_Library

ሊና ጌታቸው አየነው

በአዲስ አበባ ከተማ ነው ተወልጄ ያደግኩት። በ18 አመት እድሜዬ በታወቀውና በአሜሪካ በሚገኘው ዬል ዩኒቨርሲቲ/Yale University/የትምህርት ዕድል ተሰጥቶኝ የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ዲግሪዬን (የማስተርስ ዲግሪዬን) ለማግኘት በቅቻለሁ። ለቋንቋዎችና አለምን ለማየት ባለኝ ፍላጎት ምክንያት የዬል ዩኒቨርሲቲ ተማሪ እያለሁ የፈረንሳይኛ እና የስፓኒሽ ቋንቋዎችን በጥልቅ ሁኔታ ተምሬያለሁ። በፈረንሳይ ሀገር በፓሪስ ከተማም ቆይታ በማድረግ የፈረንሳይኛ ችሎታዬን ለማዳበር ችያለሁ። ትምህርቴን ከጨረስኩ በኋላ ከሌሎች የዬል ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ጋር ተወዳድሬ በማሸነፍ ቻንግሻ የሚባል የቻይና ከተማ ውስጥ በሚገኝ የታወቀ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ (Xiangya Medical School 湘雅医学院) ሌክቸረር ሆኜ በማገልገሌ ትምህርትን እንዴት በቀላሉ ወደ ተማሪዎች ማስተላለፍ እንደሚቻል ለመገንዘብም በቅቻለሁ። በቻይና ሀገር መኖር ከጀመርኩ በኋላ ነው ቻይንኛ መማር የጀመርኩት። ከሌላ ሀገር ከመጡ ዜጎች ይልቅ ትምህርቱ በቀላሉ ይገባኝ ነበር። ይህም የሆነው ቻይንኛ ለአማርኛ ተናጋሪዎች ስለሚቀል ነው። ቻይና እና ኢትዮጵያ ግንኙነታቸው እየጠነከረ በመምጣቱ ኢትዮጵያውያን በቀላሉ ቻይንኛ መማር እንዲችሉ ብዬ ነው ይህንን መፅሐፍ ለመፃፍ የወሰንኩት። በአሁኑ ሰዓት በቻይና እና በአፍሪካ ማህል ያለውን ግንኙነት እያጠናሁ ሲሆን ጥናቶቼም በተለያዩ የጥናትና ምርምር ተቋሞች ታትመዋል። በዚህ አጋጣሚ እናቴ ወ/ሮ ፀዳሉ በላይ እና አባቴ አቶ ጌታቸው አየነው በትምህርቴ እንድገፋ ላደረጉል ገደብ የሌለው ድጋፍ እጅግ እጅግ በጣም አመሰግናቸዋለሁ።